# Johnson & Johnson የ COVID-19 ክትባት:- ማወቅ ያለብዎት ነገሮች

## ጽሁፍ

[ለስላሳ ሙዚቃ]

[ትረካ]

**Johnson & Johnson የ COVID-19 ክትባት፡- ማወቅ ያለብዎት ነገሮች**

በአሁኑ ጊዜ የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማዕከል (CDC) ከ Johnson & Johnson የ COVID-19 ክትባት ይልቅ የ COVID-19 ክትባቶችን (Pfizer እና Moderna) ይመክራል።

**ምክረ ሃሳቦቹ እንዲዘምኑ ለምን ተደረገ?**

ባለሙያዎች እንዳገኙት ከሆነ ከ Johnson & Johnson የ COVID-19 ክትባት በኋላ አልፎ አልፎ የሚከሰተው የደም መርጋት ችግር ጥቂት ህልፈቶችን አስከትሏል። አልፎ አልፎ ይሁን እንጂ፣ አሳሳቢ ነገር ነው፣ በተጨማሪም የዚህ አይነት ተመሳሳይ ችግር የሌለባቸው ሌሎች ክትባቶች አሉ። ባለሙያዎቹ Johnson & Johnson ውጤታማነቱ ምን ያህል እንደሆነ እና ደህንነቱ ላይ ያለውን ወቅታዊ ጥናት ከገመገሙ በኋላ ምክረ ሃሳቦቹን አዘምነዋል። የሌሎችን ክትባቶችንም ደህንነት ማጥናት ቀጥለዋል እንዲሁም አስፈላጊ ከሆነ፣ ጥናቱን መሰረት አድርገው ምክረ ሃሳቦችን ያዘምናሉ። ማንኛውም አይነት ያልተለመዱ ወይም ያልተጠበቁ እንግዳ የሆኑ ከባድ የጎንዮሽ ጉዳቶች ይመረመራሉ እና መፍትሄ ይሰጣቸዋል፣ እንዲሁም ሰዎችእንዲያውቁ ይደረጋል።

**የ Johnon & Johnson ን ክትባት የተከተብኩ ከሆነስ?**

ክትባቱን ከወሰዱ ከወር በላይ ከሆንዎት የ Johnson & Johnson ን ክትባት በመውሰድዎ ያልተለመደ የደም መርጋት ሊያጋጥምዎት የሚችልበት ዕድል አነስተኛ ነው። ከወር በታች ከሆነ፣ እነዚህን ምልክቶች ይመልከቱ፡-

- የትንፋሽ እጥረት
- የደረት ህመም
- የእግር እብጠት
- የማይተው የሆድ/ የጨጓራ ህመም
- ከባድ ራስ ምታት ወይም የማይተው ራስ ምታት
- ብዥ ያለ እይታ
- መርፌ የተወጋበት ቦታ ላይ ቀለል ያለ እብጠት ወይም የደም ነጠብጣብ በቆዳ ላይ መታየት

ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ ማንኛውም እነዚህ ምልክቶች ካለብዎት፣ በአስቸኳይ የህክምና ክትትል ማግኘት ይኖርብዎታል። ለጤና ባለሙያው በቅርቡ የ Johnson & Johnson ክትባት ተከትበው እንደነበር ይንገሩት። Johnson & Johnson የ COVID-19 ክትባት በ COVID-19 ከሚመጣ ከባድ ህመም ይጠብቃል፤ ሆኖም፣ የ Johnson & Johnson ክትባት አንድ መርፌ የወሰዱ ሰዎች አሁንም ራሳቸውን ማዘመን እንዲሁም ከመጀመሪያው መርፌ ሁለት ወራት በኋላ የማጠናከሪያ ክትባት መውሰድ ያስፈልጋቸዋል። ለማጠናከሪያ ክትባት Pfizer ወይም Moderna ይመከራል።

**የተለየ አይነት ክትባት መከተብ ይኖርብኛል?**

በመጀመሪያ የወሰዱት የ Johnson & Johnson ክትባትን ከሆነ ሌላ ክትባት መጀመር አይጠበቅብዎትም። የ Johnson & Johnson ማጠናክሪያ ክትባት ከወሰዱ፣አሁን ተጨማሪ ክትባቶች መውሰድ አያስፈልግዎትም።

**አሁንም ከፈለግኩ የ Johnson & Johnson ክትባት ማግኘት እችላለሁ?**

የሚፈልጉት ክትባት የ Johnson & Johnson የ COVID-19 ክትባት ከሆነ አሁንም ማግኘት ይችላሉ። ማንኛውም ሰው ክትባቱን ከወሰደ በኋላ ያልተለመደ የደም መርጋት ሊያጋጥመው እንደሚችል ማወቅ ይኖርብዎታል። ይሁን እንጂ፣ ከ 30 እስከ 49 እድሜ ውስጥ ባሉ ሴቶች በጣም ብዙ ጊዜ የደም መርጋት ይከሰታል።ስለ ክትባቱ እና ተያያዥ ችግሮቹ ክትባቱን ካቀረበልዎት አካል ጋር ይነጋገሩ።

ራስዎን እና ሌሎችን ከ COVID-19 ለመጠበቅ ክትባት ተመራጭ መንገድ ነው። ክትባቱን ካላገኙ፣ የጤና ባለሙያ በማናገር ወይም በአቅራቢያዎ ባለ የጤና ጣቢያ በመሄድ ክትባቱን ያግኙ።

[ለስላሳ ሙዚቃ]

Minnesota Department of Health
Communications Office
PO Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
651-201-4989
health.communications@state.mn.us
www.health.state.mn.us

2/4/22 (Amharic)

*ይህን መረጃ በተለየ ቅርጸት ለማግኘት ከፈለጉ፣ በዚህ ይደውሉ:- 651-201-4989*